# የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ

ግንቦት 2001 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ፣</u>

# I. መግቢያ

ከሰፊው ህዝባዊ ትግል በድል መጠናቀቅ በኋላ በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር በመመራት በርካታ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ድሎችን በማስመዝገብ አመታትን አስቆጥረናል፡፡ እነዚህ የተገኙት ድሎች አስተማማኝ በሆነ መልኩ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የመላው ህብረተሰብ በተለይም የወጣቱ ተሳትፎ ወሳኝ እንዲሆን አያጠያይቅም፡፡ ወጣቶች በተደራጀ መልኩ የኢህአዴግን ፕሮግራሞች ማሳካት ይችሉ ዘንድ በስድስተኛው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ እንዲመሰረት መወሰኑ ይታወሳል፡፡

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ከእናት ፓርቲው በሚመነጭ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም የሚመራና በፕሮግራሙ ላይ ለሰፈሩት አላማዎች የሚታገል የወጣቶች አደረጃጀት ነው፡፡ ሊጉ ያነገባቸው አላማዎች ዲሞክራሲያዊና አብዮታዊ በመሆናቸው በተግባር ላይ ከዋሉ መላውን ህብረተሰብ በተለይ ወጣቱን ከሚገኝበት ኋላቀርነትና ድህነት አላቀው ለፍትህ ለዲሞክራሲና ለብልፅግና ያበቁታል፡፡ በመሆኑም የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለማነቃነቅና ለመለወጥ ቁልፍ መሳሪያ የሆነውን አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሮግራሙን በተግባር ላይ ለማዋል በመላ አቅሙ ይረባረባል፡፡

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ያነገባቸው አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አላማዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉት መላው ወጣት ተገንዝቧቸውና ከልብ አምኖባቸው ለተግባራዊነታቸው ሲረባረብ ብቻ ነው፡፡ ሰፊው የሃገራችን ወጣት በአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አላማዎች ዙሪያ ተሰባስቦ ለፕሮግራሙ ተግባራዊነት እንዲረባረብ ለማድረግ ደግሞ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አደረጃጀቱን እና አቅሙን በማጠናከር ወጣቱን የማንቃት፣ የማደራጀትና በተቀናጀ አግባብ ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የማሰለፍ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይጠበቅበታል፡፡

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፕሮግራሙን በስራ ላይ ለማዋል በሚያስችል ደረጃ መላውን ወጣት የማንቀሳቀስ ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት የሚችለው በራሱና በአባል የወጣት ሊጎች ውስጥ ከላይ እስከታች የሃሳብና የተግባር አንድነት ሲኖር ነው፡፡ በግንባሩ ወጣት ሊግም ሆነ በአባል ሊጎች ውስጥ ይህን የተግባር እና የሃሳብ አንድነት ለመፍጠርና ቀጣይነት ለማጎልበት እንዲቻል በአደረጃጀቱ ውስጥ አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ዲሞክራሲያዊ መድረክ ያስፈልገዋል፡፡ መተዳደሪያ ደንቡ በኢህአዴግ

ወጣቶች ሊግና በአባል ሊጎች ውስጥ የሃሳብ ትግል በነፃ መንፈስ የሚያካሂድበትን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ህጋዊና ተቋማዊ መልክ በማስያዝ አስተማማኝ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም መተዳደሪያ ደንቡ በሊጋችን ውስጥ አስተማማኝ ሁኔታን በመፍጠር ወደ ዳበረ የሃሳብና የተግባር አንድነት የሚያበቃን በመሆኑ መላ አካላትና አባላት በዝርዝር ሊገነዘቡትና ለተግባራዊነቱ ሊታገሉለት ይገባል፡፡

መተዳደሪያ ደንቡ ህጋዊና ተቋማዊ መልክ ባገኘው ዲሞክራሲ በመጠቀም የምንፈጥረው የሃሳብ አንድነት በተጠናከረ የተግባር አንድነት እንዲገለፅ ለማድረግ ያስችለናል፡፡ ዲሞክራሲ ህጋዊና ተቋማዊ መልክ መያዙ በሃሳቦች መካከል ለሚካሄድ ነፃ ትግል አስተማማኝ ሁኔታ ይፈጥራል እንጂ ልዩነትን ጨርሶ ያስወግዳል ማለት አይቻልም፡፡ የዲሞክራሲ አስተሳሰብ በግንባሩ ሊግና በአባል ሊጎች ውስጥ በፕሮግራም ጉዳዮችም ሆነ ከፕሮግራም በመለስ ባሉ ጉዳዮች ላይ ልዩነት እንዳይነሳ ወይ እንዲጠፉ ሳይሆን ልዩነቶች የግንባሩን የትግል አንድነት ሳያናጉ ስርአት ባለው መንገድ እንዲገለፁ ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

መተዳደሪያ ደንቡ ከዲሞክራሲው ጎን ለጎን የብዙሃኑ ወጣት ፍላጎት የተግባር መመሪያ እንዲሆንና በተግባር እንዲተረጎም ለማድረግ የሚያስችል ገፅታም አለው፡፡ በመሆኑም መተዳደሪያ ደንቡ በአንድ በኩል ለነፃና ግልፅ የሃሳብ ትግል አመቺ የሆነውን ዲሞክራሲያዊ መድረክ በማስፈን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለብዙሃኑ ወጣት ፍላጎት ተግባራዊ መሆን የሚያበቁ የጋራ ግዴታዎችን በውል ለይቶ በመደንገግ ሊጋችን እና የአባል ሊጎች ለጠንካራ የሃሳብና የተግባር አንድነት እንድንበቃ ያስችለናል፡፡ በመሆኑም መተዳደሪያ ደንቡ በስራ ላይ እንዲውል አጥበቀን ልንታገልለትና እንደ አይናችን ብሌን ልንጠብቀው ይገባናል፡፡

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባና ድሬዳዋ የኢህአዴግ ወጣት ሊጎች ግንባር ነው፡፡ አባል ሊጎች የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ፕሮግራም ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው በጋራ ይመራሉ፡፡ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በመተዳደሪያ ደንብ በክልልና በሀገር ደረጃ የሚሰጠው የፖለቲካ አመራር በጠራ የስራ ክፍፍል የሚመራ እንዲሆን በግንባሩ ሊግና በአባል ወጣት ሊጎች የሚኖራቸውን ሃላፊነትና የተጠያቂነት ወሰን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግም ሆነ የእያንዳንዱ አባል ሊጎች መካከል ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ በማስቻል የኢህአዴግ ፕሮግራሞችን አስተማማኝ ተፈፃሚነትን ያረጋግጣል፡፡

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ውስጥ የሚቋቋሙ ልዩ ልዩ አካላትና በነዚህ አካላት ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ የሊጉ አባላት ተግባርና ኃላፊነት ምን እንደሆነ፣ የውሳኔ አሰጣጥና አፈፃፀም ሂደት፣ እንዲሁም መዋቅሮቹ የሚጠቀሙባቸው የአሰራርና የአመራር መርሆዎች ምን እንደሆኑ በዝርዝር በማስቀመጥ ህጋዊና ተቋማዊ ስርአት ያለው ጠንካራ ግንባር ክንፍ እንድንሆን ያበቃናል፡፡ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ በሊጉ በከፍተኛ የአመራር አካላት ደረጃ የመተዳደሪያ ደንብ በሚጣስበትም ሆነ የአተረጓጎም ችግሮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ችግሮቹ እንዴት መፈታት እንዳለባቸው ግልፅ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡ በማጠቃለል መተዳደሪያ ደንባችን በሊጉ እና በአባል ድርጅቶች ሊጎች እንዲሁም በግንባሩ ሊግ የአመራር አካላትና አባላት መካከል ጠንካራ የሃሳብና የተግባር አንድነት፣ በግለሰባዊ ትስስር ምትክ በተቋማዊ አሰራር ላይ የተመሰረተ የአሰራርና የአመራር ስርአት እንዲኖረን በማድረግ ኢህአዴግ አላማዎችን በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችለናል፡፡

# I. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚመራባቸው አጠቃላይ የአደረጃጀት መርሆዎች

1. በአገራችን ውስጥ ዳሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገነባና ፈጣንና ቀጣይነት ልማት እውን ሊሆን የሚችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዓላማ በተግባር ላይ ሲውል በመሆኑ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የወጣት ሉጎች ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዓላማዎቻችን ተፈፃሚነት በፅናት የመንቀሳቀስና የጥገኝነትና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችንና ተግባራዊ እንቅስቃሴንም በፅናት የመመከት ግዴታ አለባቸው፡፡ ለሊጉ ዓላማዎችና መተዳደሪያ ደንብ ተግባራዊነት በታማኝነትና በፅናት መታገልም ኃላፊነታቸው ነው፡፡
2. ከእናት ፓርቲው ጋር የሚኖረውን ትስስር፣ አላማው ከኢህአዴግ አላማዎች የተቀዳ እንዲሆንና ድርጅታዊ አወቃቀሩ የእናት ፓርቲው አደረጃጀት የሚከተልና አጠቃላይ አመራር ለመቀበልና አክብሮ ለመስራት በሚያስችል መልኩ ሆኖ ተነፃፃሪ ነፃነት ያለው ነው፡፡
3. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዓላማ ተግባራዊነት የሚንቀሳቀስ ስለሆነ በአባልነት ሊቀበልና ሊያሰባስብ የሚችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዓላማን በግልፅ በፕሮግራማቸው ላይ የቀረፁ የወጣት ሊጎችን ብቻ

ነው። በተጨማሪም የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፕሮግራም መቀበሌ ብቻውን በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ስር ለማሰባሰብ አያበቃም፤ በተግባርም ለፕሮግራሙ ተፈፃሚነት መታገልን ይጠይቃል። በአባል የወጣት ሊጎች የሚመለመሉ አባላትም ይህንን የሚያሟላ መሆን ይኖርባቸዋል።

4. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ዓላማ ኢህአዴግ በሚያስተዳድራቸው በአንድ ክልል ውስጥና ኢህአዴግ መደበኛ ጽህፈት ቤት ከፍቶ በሚንቀሳቀስባቸው የፌደራል ከተሞች ውስጥ ሊወከል የሚችለው በአንድ የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የወጣት ሊግ ብቻ ነው። በመሆኑም በአጋጣሚ ምክንያት በአንድ ኢህአዴግ በሚያስተዳድራቸው ክልሎችና ኢህአዴግ መደበኛ ጽህፈት ቤት ከፍቶ በሚንቀሳቀስባቸው የፌደራል ከተሞች ውስጥ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ የወጣት ሊጎች ካሉና በግንባሩ ሊግ ስር መሰባሰብ ቢፈልጉ ቅድሚያ በአንድ የወጣቶች ሊግ ማጠቃለል ወይም መዋሃድ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም በአንድ ላይ ካልተጠቃለለ ሁለቱ ወይም አንድ ትክክለኛ ዓላማና አደረጃጀት ስለማይኖራቸው ነው በመሆኑም የግንባሩ ሊግ ከአንድ የኢህአዴግ ክልሎችና ኢህአዴግ በሚያስተዳድራቸው የፌደራል ከተሞች በአባልነት ሊቀበል የሚችለው አንድ የወጣት ሊግ ብቻ ነው።
5. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ዓላማ ተግባራዊ መሆን ጥቅማቸውን ሊያስከብርላቸው የሚችልና ከኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጋር ተባብረው ለመስራት ዝግጁ የሆኑ የአጋር ድርጅቶች የወጣት ሊጎችን በአጋርነት በጋራ የሚሰሩበት አደረጃጀት እንዲሁም ሊሎች ደጋፊዎችን የሚያሰባስብበት የደጋፊ አደረጃጀት ሊኖረው ይችላል።
6. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ዓላማ ተግባራዊ መሆን የሚችለው በዓላማው ቆሜለታለሁ የሚለው የወጣት ሊግ የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ውስጣዊ ህይወትና አሰራር ሲኖረው ብቻ ነው። በመሆኑም የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አንድን የወጣቶች ሊግ በአባልነት የሚቀበለው በቅድሚያ አመልካቹ የወጣት ሊግ በአባላት ተሳትፎና ውሳኔ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡ የአመራር አባላት ያለው መሆኑ፣ የአባላት ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት መከበሩ፣ የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አሰራር መስፈኑ፣ የሂስ ግለሂስና የግምገማ አሰራር ተፈፃሚነት ያለውና የወጣት ሊጉ መተዳደሪያ ደንብ የበላይነትና ተፈፃሚነት ያለውና ግልፅ ህጋዊና ፍትሃዊ አሰራር የሰፈነበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

7. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች፣ የአዲስ አበባና ድሬደዋ የኢህአዴግ ወጣት ሊጎች መገለጫ የሆነ የኢህአዴግ ክንፍ እንደመሆኑ መጠን የወጣት ሊጎች የኢህአዴግ ወጣት ሊጉን የሚቀላቀሉት አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሙንና መተዳደሪያ ደንቡን ተቀብለው ነው። በመሆኑም ከኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የተለየ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለማዊ ህልውና አይኖራቸውም። ከዚህ በመነሳት የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ዓላማዎች በየክልላቸው የማስፈፀምና የኢህአዴግና የወጣቶች ሊግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለባቸው። ሆኖም ግን እያንዳንድ የኢህአዴግ ወጣት ሊግ አባል፣ የኢህአዴግ ወጣት ሊግን ፕሮግራምና አጠቃላይ እቅዶች ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማጣጣም፣ ውስጠ ድርጅት ህይወቱን የማከናወን፣ ወደ ኢህአዴግ ወጣት ሊግ ልዩ ልዩ አካላት የሚልካቸውን ተወካዮች ራሱ መርጦ የመልክና ሲፈልግም የመቀየር ነፃነት ይኖረዋል። የኢህአዴግ ወጣት ሊግን በፍላጎት እንደተቀላቀለው ሁሉ በአባልነት መቀጠል ባልፈገበት ጊዜም ለቆ የመውጣት ነፃነቱ የተጠበቀ ነው። ሆኖም የኢህአዴግ ወጣት ሊግን ለቆ የመውጣት ጉዳይ የሚፈፀመው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በዝርዝር በሰፈሩት አንቀፆች መሰረት ነው።

8. የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ አንድነቱን በመጠበቅ ተጠናክሮ ፕሮግራሙን ማሳካት የሚችለው በአባል የወጣቶች ሊጎች መካከል እኩልነት ሲኖር ነው። የበርካታ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሊጎች ግንባር እንደመሆኑ መጠን በሊጎቹ መካከል የሚኖር ግንኙነት ከእኩልነት ውጭ ልታሰብ የሚችል አይሆንም። በመሆኑም አባል የወጣት ሊጎች በሙሉ ተመሳሳይ መብትና ግዴታ ሊኖሯቸው በጋራ ጉዳዮች ላይ በእኩልነት የመምከር፣ በውሳኔ አሰጣጥ የመሳተፍና በግንባሩ ሊግ አመራር አካላት ውስጥ የኢህአዴግ አባል ድርጅት ሊጎች በእኩልነት የመወከል መብት ይኖራቸዋል።ሆኖም የአዲስ አበባና የድሬደዋ የኢህአዴግ የወጣቶች ሊጎችን በተመለከተ የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ ምክር ቤት በሚያወጣው የአሰራር መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል።

# ምዕራፍ አንድ

# ጠቅላላ

## አንቀፅ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መስራች ጉባኤ ፀድቆ የወጣ «የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብ» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 2

## ስያሜ

ሊጉ "የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ወጣቶች ሊግ" (የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ) ተብሎ ይጠራል፡፡

## አንቀፅ 3

## አድራሻ

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ከተማ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይኖሩታል፡፡

## አንቀፅ 4

## አርማና ማህተም

1. ሊጉ ስራውን ህጋዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚያስችለው አርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡
2. አርማው በሃገራችን ያሉ ወጣቶች በዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በሰላምና በልማት ዙርያ ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያጠናክር የወጣቶችን አንድነት የሚያጎለብት መልዕክት ያለው ሆኖ ዝርዝሩ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 5

## የአርማ ትርጉም

1. **የአርማው ይዘት ፡-**
    1.1 የኢህአዴግ አርማ
    1.2 የወንድንና ሴትን ምስል የያዘ
    1.3 ቀለም ሠመያዊ መሆንን ያካተተ ነው ፡፡

2. የአርማው ትርጉም ፡-

**የኢህአዴግ አርማ**

- የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችን /ግንባር/ ቀደምትነት ያዘለ
- ቀዩ መደብ የትግሉን አለመቋረጥ የሚያሳይ መሆን

2.1 የወንድና የሴት ምስል ፡-

- በኢህአዴግ የወጣት ሊግ አርማ መሆኑን ፣
- ወጣት ሲባል ወንድንና ሴትን ያቀፈ መሆን ፣
- የእጆች መጣመር ፆታዊ ልዩነት የሌለውና በጠንካራ /ዴሞክራሲያዊ/ ትስስር ትግሉን በጽናት የመምራት ፣

2.2 የወንዱና የሴቷ ምስል ቀለም ፡-

- ሠመያዊ ቀለም ወጣቱ ኃይል ብሩህ አምዕሮ ያለው እና እውቀቱ / ችሎታው/ ያልተወሰነ መሆን ፣
- ሠመያዊ ህብር ምልከታው የከርሰ ምድር ሀብት / ብልጽግናን/ የሚወክል በመሆኑ ወጣቱ ተወክሏል ።

## አንቀፅ 6

## የሊጉ ዓላማዎች

የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. የኢህአዴግ ፕሮግራም በህዝብ ውስጥ ሰርፆ በስራ እንዲተረጎም እና በቀጣይነት መላው ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን መጣር፣
2. ወጣቱ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊና ከስርዓቱ ደረጃ በደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻልና የኢህአዴግ አላማዎች ለማሳካት መታገል፣
3. ወጣቶች ሀገር ተረካቢ ዜጋ እንደመሆቸው መጠን በጥሩ ስነ ምግባር ተኮትኩተው ለሃላፊነት የሚበቁ እንዲሆኑ ማስቻል፣
4. በወጣቶች ውስጥ የመቻቻልና የዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብርና ለጋራ ጥቅም እንዲቆሙ ለማድረግ፣

5. ወጣቱ የስራ ባህሉ ዳብሮ ስራ ፈጣሪ በመሆን ራሱን እና ሀገሩን ከድህነትና ኃላቀርነት ለማውጣት የሚታገል እንዲሆን ማድረግ፣
6. ወጣቱ አለም አሁን ከደረሰችበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ጋር እንዲራመድ የፈጠራ ዝንባሌው እንዲጎለብት እና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል፣
7. ወጣቶች ዴሞክራሲያዊ ብሄራዊ አንድነታቸውን በመጠቀም የመተሳሰብና የመረዳዳት ባህል ማጎልበት በሃገራዊ ጉዳዮች ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣
8. ወጣቱ ህገ-መንግስቱ ያጎናፀፈውን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በትክክል በመገንዘብ የተጎናፀፈውን ነፃነቶች እንዲጠበቁለት በስራ እንዲተረጎሙ የእራሱን ሚና መጫወት እንዲችል ማድረግ፣
9. በኢህአዴግና በወጣቱ መሃል መሸጋገርያ ድልድይ በመሆን ቀጣይ ሃገር ተረካቢ አብዮታዊ ዲሞክራት ትውልድ መፍጠር የአብዮታዊ ዲሞክራሲን አላማ ህልውና በቀጣይነት ማረጋገጥ።
10. ኪራይ ሰብሳቢነትን መታገል፤ልማታዊነትና ዴሞክራሲያዊነት ለማንገስ መታገል።
11. ህብረተሰቡ ያፈራቸውን ግንባር ቀደም ወጣቶችን ማሰባሰብና ማጠናከር፤ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አላማዎች እና በወጣቱ ጥያቄዎች ዙሪያ ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ መታገል።

## አንቀፅ 7

## ስለሊጉ ህጋዊነት

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚከተሉት ህጋዊነቶች ይኖሩታል።

1. በስሙ ውል የመዋዋል።
2. የመክሰስም ሆነ የመከሰስ።
3. የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት የማፍራት፣ በባለቤትነት የመያዝ፣ የማንቀሳቀስ፣ ለሌላ ወገን የማስተላለፍ፣ ስጦታ የመቀበልና የመስጠት።
4. የባንክ ሂሳብ የመክፈትና የማንቀሳቀስ
5. ሊጉ የቆመለትን አላማ መሰረት አድርጎ ለስራው መዋቅሮችን የመዘርጋት።
6. የሊጉን አላማ ለማሳካት ከሚረዱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነት የመፍጠር።

# አንቀፅ 8
# ግንኙነት
## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ እና ኢህአዴግ የሚከተለው ግንኙነት ይኖራቸዋል።

የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የኢህአዴግ ክንፍ ነው። በመሆኑም በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አላማዎች ይመራል። ሊጉ ከእናት ድርጅቱ ጋር ያለው ግንኙነት የእናት ድርጅቱን አመራር በመቀበል ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ኢህአዴግን በመወከልም በወጣቱ ውስጥ የሚሰሩ ስራዎችን የሚሰራ ሆኖ የሚከተሉት ግንኙነቶች ይኖራቸዋል።

1. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በአባላቱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እና የኢህአዴግን ፕሮግራም በእምነት ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ የፖለቲካ ድርጅቱ አካል ነው፣
2. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ራሱን የቻለ የወጣት አደረጃጀት ሆኖ ከኢህአዴግ መዋቅር ጋር በየደረጃው ተሳስሮ የሚዋቀር ሲሆን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አላማና ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ አካሄድ ይኖረዋል። ኢህአዴግ የሚመራባቸውን መስመሮችና መርሆዎች በፅምነት ተቀብሎ ለተግባራዊነታቸው በፅናት ይታገላል፣
3. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በየደረጃው በኢህአዴግ ጥላ ስር የድርጅቱን ውሳኔዎች ያከብራል። ከሊጉ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በስራ ላይ ያውላል፣
4. የሊጉ ህልውና በእናት ፓርቲው ህልውና ላይ የተመሰረተ መሆኑን በእምነት በመቀበል ለእናት ፖርቲው ህልውና ማረጋገጥ፣ ከዚሁ ጋር ለራሱ ህልውና መረጋገጥ በአጠቃላይ ለኢህአዴግ አላማዎች መረጋገጥ ይታገላል።

# አንቀፅ 9
# የሊጉ ልሳን

1. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሊጉን አቋሞችና እንቅስቃሴዎች ይፋ የሚያደርግበት የራሱ ልሳን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በሊጉ ምክር ቤት ይወሰናል።

# ምዕራፍ ሁለት

# የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አደረጃጀትና የአሰራር መርሆዎች፡-

## አንቀፅ 10

የጋራ አሰራርና የግለሰብ ሀላፊነትን በተመለከተ

1. በየደረጃው የሚገኙ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አካላት ማንኛውንም ውሳኔ የሚያሳልፉት በጉዳዩ ላይ በጋራ ከተወያዩ በኋላ በድምፅ ብልጫ ይሆናል፣
2. አንድ ሰው አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል:: ለውሳኔ የቀረበ ሀሳብ የጋራ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው ከተገኘው ምልዐተ ጉባኤ 50%+1 እና ከዚያ በላይ ድምፅ ካገኘ ነው:: ተሰብሳቢው በእኩል ድምፅ ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምፅ አሸናፊ ይሆናል፣
3. በየትኛውም አካል ስብሰባ ላይ ምልዐተ -ጉባኤ ተማልቷል የሚባለው ከጠቅላላ የስብሰባው ተከፋዮች 50%+1 ሲገኙ ነው፣
4. 50%+1 እና ከዚያ በላይ ድምፅ ያገኘ የውሳኔ ሀሳብ በወሰነው አካልና ከሱ በታች ባሉ አካላትና አባላት በሙሉ ተፈፃሚ ይሆናል፣
5. በማንኛውም የኮሚቴ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ለኮሚቴው አባላት በተናጠል ወይም ደግሞ ከኮሚቴው በታች ላሉ አካላትና አባላት በሚሰጥ የጋራ ወይም የተናጠል ሀላፊነት ይሆናል፣
6. ማንኛውም የበታች ኮሚቴ ወይም የበታች ኮሚቴዎች አባል ከበላይ አካል የመጣለትን ውሳኔ የመፈፀም ግዴታ አለበት፣
7. በኮሚቴ ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ወይም ያልተስማማ አባል ውሳኔዎቹን እየፈፀመ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ህጋዊ በሆነ መንገድ የመጠየቅ መብት አለው፣
8. በማናቸውም የውሳኔ ሀሳብ ላይ ከተሰብሳቢው አባል 1/3ኛ በሚያህሉት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ከቀረበ እንደገና የመታየት ጥያቄው ለውይይት ክፍት ይሆናል:: ከ50%+1 በላይ የሆኑት እንደገና መታየት አለበት ብለው ከወሰኑ ጉዳዩ እንደአዲስ ታይቶ ይወሰናል፣
9. በአንድ መድረክ በተወሰነ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ቀርቦ በዚያው መድረክ ተቀባይነት ካላገኘ ተደጋጋሚ አቤቱታዎች አይቀርቡም:: በጉዳዩ ላይ አቤቱታ

ማቅረብ የሚቻለው ውሳኔውን በተግባር እየፈፀሙ በሂደት በሚከፈት የስብሰባ አጋጣሚ ወይም የፅሁፍ ፊርማ በማሰባሰብ ብቻ ይሆናል፣

10. እንደገና ይታይልን በሚል ጥያቄ የወሰነው አካል በስብሰባ ላይ ባለበት በቃል ወይም በፅሁፍ፣ ወሳኙ አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዩ ከላይ በተራ ቁጥር 7 ላይ በቀረበው መሰረት ይታያል፡፡ ወሳኙ አካል ከተበተነ ደግሞ በፅሁፍ አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በፅሁፍ የሚቀርብ አቤቱታ የሚቀርበው ህጋዊነትና ግልፅነት በተላበሰ አኳኋን ይሆናል፡፡ አቤቱታ አቅራቢው ግለሰብ አቤቱታውን በፅሁፍ አዘጋጅቶ ለአካሉ ሰብሳቢ ያስረክባል፡፡ ሰብሳቢው አቤቱታውን ወደ ሚመለከታቸው አባላት ሁሉ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በማሰራጨት አቤቱታውን የሚደግፉ ሁሉ እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡ ከሚመለከታቸው አባላት ውስጥ 1/3ኛው ከፈረሙ ጉዳዩ በሚቀጥለው መደበኛ ስብሰባ ወይም ደግሞ እንደአመችነቱ ቀደም ብሎ በሚጠራ አስቸኳይ ስብሰባ ላይ እንዲታይ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 11

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አሰራሮች በግልፅነትና በተጠያቂነት መርህ ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ፡፡

1. የበላይ አካላት ውሳኔዎች በተለየ ሁኔታ በምስጢር ተጠብቀው እንዲቆዩ ካልተወሰነ በስተቀር በተዋረድ ለአባላት ይገለፃሉ፣
2. በተለየ ሁኔታ በምስጢርነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉ ጉዳዮች በሊጉ ላይ ጉዳት የማስከተል ፋይዳ ያላቸው ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡
3. በየደረጃው የሚገኙ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የአመራር አካላት የስራ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት በተመደበላቸው ወቅት ለበላይ አካላት ያቀርባሉ፣
4. በየደረጃው የሚገኙ አካላት በወሰኗቸው ውሳኔዎች ሁሉ ሀላፊነት ይወስዳሉ፡፡ በተጨማሪም ሀላፊነትን ባለመወጣት ወይም ከተሰጠ ሀላፊነት ውጭ ከተሰማሩ ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል፣
5. ተጠያቂነቱ እንደሁኔታው በኢህአዴግ ወጣት ሊግ፣ በአባል ሊጎች ወይም በአገሪቱ ህጎች ክልል ሊፈፀም ይችላል፡፡

## አንቀፅ 12

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ተግባራት በክልሎችና በፌደራል ከተሞች ደረጃ ተፈፃሚ የሚሆኑት በአባል ሊጎች አማ?ኝነት ይሆናል፡፡

1. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በአገር ደረጃ እንዲፈፀም ያወጣው ፕሮግራም፣ የሚወስናቸው ውሳኔዎችም ሆነ የሚያወጣቸው እቅዶች በክልሎችና በፌደራል ከተሞች ተፈፃሚ የሚሆኑት በአባል ሊጎች አማካይነት ይሆናል፣
2. አባል ሊጎች አገራዊውን ውሳኔና መሰረታዊ የአፈፃፀም አቅጣጫ በአካባቢያቸው ተፈፃሚ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ሆኖም አገራዊ ውሳኔዎችንና የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማጣጣምና የመፈፀም ድርጅታዊ ነፃነት አላቸው ፡፡
3. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በክልሎችም ሆነ በፌደራል ከተሞች ውስጥ ከአባል ሊጎች መዋቅር የተለየ ሌላ መዋቅር አይዘረጋም፡፡ ሆኖም በጊዜያዊነት ተልእኮ የመፈፀም ሀላፊነት ወስደው በአካባቢው ከሚገኘው ብሄራዊ ድርጅት ሊግ ጋር በቅንጅት የሚንቀሳቀሱ ጊዜያዊ ቡድኖችን ወይም ግለሰቦችን መላክ ይችላል፣
4. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በአባል ወጣቶች ሊግ ውስጥ ከተናጠል የሊጎቹ አቅም በላይ የሆነ ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም በምክር ቤቱ ውሳኔ መሰረት ችግር ያጋጠመውን ሊግ በልዩ ልዩ አግባቦች ለማገዝ ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ እገዛ የሊጉን ጥንካሬና ራስን ችሎ የመቆም ሂደት በሚያጠናክር መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

## ???? 13

## ?? ??? ? ???? ??? ? ????? ?? ??????

በፌደራል መንግስት ተቋማት የወጣቶች ሊግ አደረጃጀት በተመለከተ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይፈፀማል፡፡

## አንቀፅ 14

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ከሌሎች የወጣቶች አደረጃጀቶች ጋር ስለሚያደርገው ግንኙነት

1. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በሃገሪቱ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ህገ-መንግስቱን ተቀብለውና አክብረው ከሚሰሩ በየደረጃው ከሚገኙ የወጣት አደረጃጀቶች ጋር ሃገራዊ ጉዳዮችና በወጣቱ አጀንዳ ላይ አብሮ መስራት ይችላል፣
2. በሃገራችን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ አስተዋፅኦ ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ የተለያዩ ማህበራት ጋር በፌደሬሽን እና ኮንፌዴሬሽን ተደራጅቶ ሊሰራ ይችላል፣

## አንቀፅ 15

## ስለ አጋር ድርጅት የወጣቶች ሊጎች

የሚከተሉትን የሚያማላ ማንናቸውም የአጋር ድርጅቶች ወጣት ሊግ ከኢህአዴግ ወጣት ሊግ ጋር በአጋርነት መስራት ይቻላል፣

1. የሀገሪቱን ህገ-መንግስት የሚቀበልና ለተግባራዊነቱ የሚታገል፡፡
2. ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ በሚደረገው እንቅስቃሴ ከኢህአዴግ ወጣት ሊግ ጋር ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ የሆነ
3. በአካባቢው ወጣቱን በማንቀሳቀስ ከድህነትና ኃላቀርነት ለማላቀቅ በሚደረገው ትግል የመሪነት ሚና የሚጫወት
4. ጥገኛ አስተሳሰብና ድርጊቶችን በመታገልና ውስጠ ድርጅታዊ አሰራሩን ዲሞክራሲያዊ በማድረግ በኩል ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኝ
5. ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ አላማዎች በጎ አመለካከት ያለው

## ምዕራፍ 3

## አባልነት፣ የአባልነት መብትና ግዴታ 13

## አንቀጽ 16

## አባልነት

## የኢህአዴግ ወጣት ሊግ አባል ስለመሆን

1. የኢህአዴግንና የወጣት ሊጉን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለና ለተግባራዊነቱ በፅናት የሚቆምና የሚታገል፣
2. የተሟላ ውስጣዊ ዴሞክራሲያዊ አሰራር ያለውና ተግባራዊ የሚያደርግ፣
3. የኢህአዴግ አባል ድርጅት የወጣቶች ሊግ የሆነ ከአንድ ብሄራዊ ድርጅት አንድ የወጣት ሊግ ብቻ ሆኖ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ኢህአዴግ የወጣት ሊጎች የግንባሩ ሊግ አባል ይሆናሉ፣
4. በሊጉ ህጎችና መመሪያዎች መሰረት እንደአስፈላጊነቱም በተለያዩ የሊጉ መዋቅሮችና ስራዎች ውስጥ በመሳተፍ ተጨባጭ አስተዋፅኦ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ፣
5. ለሊጉ ተግባሮች ማስፈፀምያ በሚወጣው መመሪያ መሰረት መዋጮ ለመክፈል ዝግጁ የሆነ።

## አንቀፅ 17

## የአባል ሊጎች መብት

1. ሁሉም የብሄራዊ ድርጅቶች ወጣት ለጎች እኩል መብት ያላቸው ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፣
2. በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ መተዳደሪያ ደንብና አሰራር መሰረት በውክልና የሚሞሉ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ የብሄራዊ ድርጅት ወጣት ሊግ በእኩል የሚወከሉ ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬደዋ ወጣቶች ሊግ በኢህአዴግ መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፣ ፣
3. በተዋጽኦ ድምፅ መሞላት ከሚኖርባቸው ቦታዎች ውጪ በደንቡ መሰረት በምርጫ ለሚወሰኑ የሃላፊነት ቦታዎች ዕጩዎችን የማቅረብ ወይም ከመካከሉ መርጦ የመመደብ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመቀየር፣

4. ደንቡ በሚፈቅደው አሰራር መሰረት ማንኛውንም ሃሳብ በወጣት ሊግ ውስጥ የማራመድና የማሰማት፣
5. በራሱ ውስጣዊ አሰራር መሰረት በነጻነት የመስራት፤ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን በሚመለከቱ ጉዳዮች በጋራ የመወሰን፣
6. በግንባሩ ወጣቶች ሊግ ንብረቶች በጋራ የመጠቀም
7. አባልነቱን ባልፈለገበት ወቅት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተወሰነው መሰረት በማንኛውም ጊዜ የመልቀቅ መብት አለው::

## አንቀፅ 18

## የአባል ሊጎች ግዴታ

ማንኛውም የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል::

1. የኢህአዴግና የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች ውሳኔዎችና እቅዶችን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ፣
2. የኢህአዴግና የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ አሰራርና የአመራር መርሆዎችን ማክበርና መከተል፣
3. የኢህአዴግና የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ ደህንነትና ምስጢር የመጠበቅ፣
4. የአባል ሊጎች አብዮታዊ አንድነት የሚሸረሽሩ አመለካከቶችና ተግባሮችን መታገል
5. በአባል ሊጎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በእኩልነት የማጎልበትና የማጠናከር፣
6. የኢህአዴግ ወጣት ሊግ እንደ አባል ሊግ ተወክሎ በሚሳተፍባቸው አካላት መደበኛም ሆነ አስቸኳይ ስብሰባዎች የመሳተፍ፣ ምልአተ ጉባኤ አለማጓደል::

## አንቀፅ 19

## ከአባልነት ስለመሰረዝና አባልነትን በራስ ፈቃድ ስለመተው

1. በጥፋት ከአባልነት ማገድና መሰረዝ

1.1. ከላይ በአንቀጽ 18 የተዘረዘሩትን ግዴታዎች በተሟላ ሁኔታ የማይፈጽም አባል ሊግ ከኢህአዴ.ግ ሊግ አባልነት በጊዚያዊነት ሊታገድ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊወገድ ይችላል::

1.2. በጥፋተኛው አባል ሊግ ላይ ከአባልነት የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔ የሚተላለፈው በቅድሚያ ሂስ ቀርቦለት ግዴታውንም እንዲያሟላ እድል ተሰጥቶት ጥፋቱን ሳያስተካክል ከቀረ ብቻ ነው ፡፡

1.3. አንድ አባል ሊግ ከአባልነት የማገድ ወይም የመሰረዝ ውሳኔ የሚተላለፈው በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

1.4. ከአባልነት የማገድ ወይም የመሰረዝ እርምጃ የተወሰደበት አባል ሊግ ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ቁጥጥር ኮምሽን አቤቱታ የማቅረብና ጉዳዩ በጉባኤ እንዲታይለት የመጠየቅ መብት አለው፡፡ ጉባኤው ጉዳዩን የሚመለከተው ከሆነ የታገደው ወይም የተሰረዘው አባል ሊግ ተወካዮች አቤቱታቸውን ለማቅረብ ብቻ በጉባኤው ላይ እንዲገኙ ይደረጋል፡፡ በጉዳዩ ላይ ጉባኤው የሚያስተላልፈው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፣

1.5. ከአባልነት የተሰረዘ አባል ሊግ በሂደት ስህተቱን አርሞ ወደ አባልነቱ ለመመለስ ሲጠይቅ ሁኔታው በጉባኤ ታይቶ ተቀባይነት ካገኘ እንደገና አባል ሊሆን ይችላል፣

2. አባልነትን በራስ ፈቃድ ስለመተው

2.1. ማንኛውም የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አባል የሆነ ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት አሳውቆ በፈለገው ጊዜ ሊጉን መልቀቅ ይችላል፡፡

2.2. ከላይ 2.1. የተጠቀሰው መብት ቢኖርም የመልቀቁ ውሳኔ የሚፀናው እለቃለሁ ባለው አባል ሊግ ጉባኤ ሲወሰን ነው ፡፡

2.3. ከላይ በ2.1. እና 2.2. የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ሌሎች አባል ሊጎችም በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚችሉበት እድል የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡

3. ከአባልነት ማገድ ፣መሰረዝና አባልነትን ስለመተው በተመለከተ የኢህአዲግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

# ምዕራፍ 4

# የወጣቶች ሊግ መዋቅር

## አንቀፅ 20

## ጠቅላላ

የሊጉ አወቃቀር የኢህአዴግን ድርጅታዊ አወቃቀር ተከትሎ የሚሄድ ይሆናል፣

## አንቀፅ 21

## የሊጉ መዋቅራዊ ቅርፅ

## የወጣቶች ሊግ አመራር አካላትና ልዩ ልዩ መዋቅሮች

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. ምክር ቤት
3. ስራ አስፈፃሚ
4. ሊቀ መንበር
5. ምክትል ሊቀ መንበር
6. የቁጥጥር ኮሚሽን
7. ጽህፈት ቤት

## አንቀፅ 22

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጉባኤ

1. የጠቅላላ ጉባኤው አጠራርና አመሰራረት

   1.1 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጉባኤ ከሁለት ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ተኩል ባለው ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል። ሆኖም አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥም ምክር ቤቱ ጉባኤውን እስከ ስድስት ወር ማራዘም ይችላል፣

   1.2 የጉባኤው ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የወጣቶች ሊግ በእኩል ድምፅ በሚወከሉ ጉባኤተኛ ይካሄዳል። የምክርቤት አባላትና የቁጥጥር ኮሚሽን አባላት በቀጥታ ይሳተፋሉ፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ተሳትፎ በልዩ ሁኔታ የሚወከል ይሆናል፣

1.3 የጉባኤው አባላት ከተወከሉብት ጉባኤ እስከሚቀጥለው ጉባኤ ድረስ ባለው ጊዜ በቀዳሚ ጉባኤተኛነትይቆያሉ፡፡

1.4 ለጉባኤው የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በሚቋቋም የጉባኤአዘጋጅ ኮሚቴ አማካኝነት ይካሄደል፡፡

1.5 የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና ከኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት እንዲሁም ከአባል ሊጎች አጀንዳ ይሰበስባል

1.6 የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው ተሳታፊዎችን ቁጥርና ስብጥር አስመልክቶ መነሻ ሃሳብ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1.7 ለኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ የሚወከሉ ጉባኤተኞች በየአባል ሊጎች ጉባኤ ይመረጣሉ፡፡ ሆኖም ቀደም ብሎ ማካሄድ ያልቻለ አባል ሊግ ከታች ጀምሮ በሚደረግ ምርጫ ጉባኤተኛ ሊያስወክል ይችላል፡፡

2. **አስቸኳይ ጉባኤ፡-** የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ ሲወስን ወይም ከአባል ሊጎች ግማሽ ያህሉ ሲጠይቁ ወይም ደግሞ የቀዳሚ ጉባኤ አባላት ጥያቄ አቅርበው ከቀዳሚ ጉባኤተኛው 50%+1 የድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ አስቸኳይ ጉባኤ ይጠራል፡፡

2.1 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ቁጥጥር ኮሚሽን የቀዳሚ ጉባኤ አባላትን 1/3ኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸካይ ጉባኤ እንዲጠራ ለማድረግ ይችላል፡፡

2.2 አስቸኳይ ጉባኤ በሚጠራበት ጊዜ አስቀድሞ በተካሄደው መደበኛ ጉባኤ የተካፈሉ ጉባኤተኞች በቀጥታ እንዲሳተፉ ይደረጓል፣ የሚጎደል የሰው ሃይል ቢኖርም ምልዐተ ጉባኤን የሚያዛባ እስካልሆነ ድረስ አዲስ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ምርጫ አይካሄድም፡፡

2.3 የአስቸካይ ጉባኤው ምልዐተ ጉባኤ 50%+1 ነው፡፡

3. የጠቅላላ ጉባኤው ተግባርና ሃላፊነት

3.1 ጉባኤው የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የመጨረሻው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው፡፡

3.2 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ፕሮግራምና መተዳደርያ ደንብ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ እንደአስፈላጊነተም ይቀይራል፡፡

3.3 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚመራባቸውን አገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂ ይነድፋል ፡፡

3.4 እስከ ቀጣይ ጉባኤ ድረስ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚያከናውናቸውን አጠቃላይ ተግባራትና ዕቅድ ያፀድቃል፡፡

3.5 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት፣ የስራ አስፈፃሚና የቁጥጥር ኮሚሽን ኮሚቴ አባላትን ቁጥር ይወስናል፣ ሪፖርት አድምጦ ይገምግማል፣ የአባላትን ቁጥር ይወስናል፣

3.6 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤትና የቁጥጥር ኮሚሽን ያዘጋጅቱን ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ ይገምግማል፣ ውሳኔም ይሰጣል፡፡

3.7 ከምክር ቤቱ በሚቀርብለት ሪፖረት መሰረት ሙሉ አባልነትን ያፀድቃል፡፡ ከአባልነት የመሰረዝ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

4. የጠቅላላ ጉባኤው አሰራር

4.1 ጉባኤው በፕሬዝዲየም ይመራል፣ የፕሬዚዲየሙ አባላትም የአባል ሊጎች ሊቀ-መናብርት ይሆናሉ፣

4.2 ጉባኤው መደበኛ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴው አማካይነት የጉባኤ ዝግጅቱን በተመለከተ ሪፖርት ቀርቦ እንዲጸድቅ ይደረጋል።

4.3 በጉባኤው ላይ ለውይይት የሚቀርቡ አጀንዳዎች አስቀድመው በጉባኤተኛ እንዲጸድቁ ይደረጋል።

## አንቀፅ 23

### የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት አመሰራረት፣ ተግባርና ሀላፊነት እና አሰራር

1. የምክርቤቱ አመሠራረት

   1.1. ምክር ቤቱ ከጉባኤ ቀጥሎ ያለ ከፍተኛ የአመራር አካል ነው፣

   1.2. ከሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅት ሊጎች ጉባኤው በወሰነው የምክር ቤት አባላት ቁጥር በእኩል ድምፅ ይወከላሉ። አዲስ አበባ ድሬዳዋ ወጣቶች ሊጎች በተለየ ሁኔታ ውክልና ይኖራቸዋል፣

   1.3. የእያንዳዱ አባል ሊግ ማእከላዊ ኮሚቴ የወከላቸውን የምክር ቤት አባላትን የማውረድና በምትካቸው ሌላ መርጦ የመተካት መብት ይኖረዋል፣

   1.4. የምክር ቤቱ ተጠሪነት ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጉባኤ ነው።

2. የምክር ቤቱ ተግባርና ሃላፊነት

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል

2.1. ከአንድ ጉባኤ እስከሚቀጥለው ጉባኤ ድረስ ሊጉን በበላይነት ይመራል።

2.2. የጉባኤውን ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ አገር አቀፍ ሚናና ትርጉም ባላቸው ጉዳዮች ላይ የወጣት ሊጉን በሚመለከት ፖሊሲዎችን ያወጣል ፣ እቅዶች ይነድፋል።

2.3. በሊጉ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም በሚሹ አከራካሪ ነጥቦች ላይ ውሳኔ ይሰጣል

2.4. መተዳደሪያ ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመርያዎችን ያወጣል ያፀድቃል፣

2.5. ለሊጉ የስራ ቅልጥፍና አስፈላጊ የሆኑ መዋቅሮችን ያደራጃል ያሻሽላል፣

2.6. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት ያዳምጣል ይገመግማል ውሳኔ በሚሹ ነጥቦች ላይ ይወስናል፣

2.7. በምክር ቤቱ አባላት 2/3ኛ ድምፅ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ እጩ አባልነትን ያፀድቃል። በተግባር ለሙከራ ጊዜ አባልነት ብቁ ሆኖ ያልተገኘ ሊግ ከእጩ አባልነት ይሰረዛል።

2.8. የአባልነት ግዴታውን ያላሟላ ሊግ እስከ ጉባኤ ድረስ ከአባልነት ያግዳል። ከአባልነት የሚሰረዘው በጉባኤው ውሳኔ ይሆናል።

2.9 ጥፋት በፈፀመ የምክር ቤቱ አባል ላይ በ2/3ኛ ድምፅ በጊዜያዊነት ከምክር ቤት አባልነት የማገድ እርምጃ ይወስዳል። ውሳኔው የምክር ቤቱ በአባል ወጣት ሊጎች ከፀደቀ በኃላ የጸና ይሆናል፣

2.10 ኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ይመርጣል፣

2.11 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል።

3. ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባና አሰራር

3.1 የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየ6 ወሩ ይካሄዳል።

3.2 ከላይ በ«3.1» የተጠቀሰው ቢኖርም በ1/3ኛ የምክር ቤቱ አባላት ወይም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጥያቄ ሲቀርብ ምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል።

3.3 በምክር ቤቱ በጋራ የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ በሁሉም አባል ሊጎች ተፈፃሚ ይሆናል።

3.4 የምክር ቤቱ ስብሰባ በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሊቀመንበር ይመራል፣

3.5 በተናጠል አባል ሊጎችን የሚመለከት ጉዳይ እንደአስፈላጊነቱ በሚመለከተው አባል ሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴ ብቻ ሊወሰን ይችላል፣

## አንቀፅ 24

## የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አመሰራረት፣ ተግባርና ሃላፊነትና አሰራር

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አመሰራረት፣

1.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሁሉም የኢህአዴግ አባል ድርጅት ወጣት ሊጎች የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በእኩል ቁጥር ይቋቋማል ።ሆኖምየአዲስ አበባና 20

የድሬደዋ የኢህአዴግ ወጣት ሊጎችን በተመለከተ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡

1.2. የእያንዳንዱ አባል ሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተወካዮቹን ሊቀይር ይችላል፣

1.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት ነው፡፡

1.4. ከየአባል ሊጎች የተወከሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተጠሪነታቸው ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለየተወከሉበት ወጣቶች ሊግ ማዕከላዊ ኮሚቴዎች ነው፣

2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተግባርና ሀላፊነት

2.1 የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች ያስፈፅማል፡፡

2.2 የልዩ ልዩ የጋራ አካላትን ስራዎችና እንቅስቃሴዎች ይመራል፡፡

2.3 ከአባል ወጣት ሊጎች ጋር በመመካከር ለጋራ ተቋማት የሚያስፈልግ የሰው ሃይል ምደባ ያካሂዳል፡፡

2.4 ለምክር ቤቱ ስበሰባዎች ሪፖርትና አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡

2.5 እንደአስፈላጊነቱ ጊዜያዊ አካላትን አዋቅሮ ያሰራል፡፡

2.6 የምክር ቤት ውሳኔዎችን ለማስፈፀም የሚረዱ የስራ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

2.7 በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ስም ውል ይዋዋላል፡፡

2.8 ከሁሉም አባል ሊጎች የሚወከሉበት የጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ያቋቁማል፣ ዝርዝር የስራ መመሪያም አዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡

3. ስለ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባና አሰራር

3.1 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መደበኛ ስበሰባ በየ3 ወሩ ይካሄዳል፡፡

3.2 ሊቀመንበሩ ወይም ምክትል ሊቀመንበሩ፣ እንዲሁም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አባላት 1/3ኛው አስቸኳይ ስበሰባ እንዲጠራ ሲጠይቁ አስቸኳይ ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣

3.3 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ስብሰባ አስቸኳይ ጉዳዮች ከሌሉ በቀር አስቀድሞ በተዘጋጁ ጽሑፎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

3.4 በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ በሁሉም የኢህአዴግ አባል ሊጎች ተፈፃሚ ይሆናል፣

3.5 የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ስብሰባ በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሊቀመንበር ይመራል፡፡

## አንቀጽ 25

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሊቀመንበር ተግባርና ሃላፊነት

1. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የምክር ቤትና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል።
2. የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል። የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን እንቅስቃሴ ያስተባብራል።
3. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል።
4. የስራ ሪፖርቱን ለስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ያቀርባል፣ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች አጀንዳ ያዘጋጃል።
5. የወጣት ሊጉን የጽህፈት ቤት ስራዎች በበላይነት ያስተባብራል።
6. በምክር ቤቱና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሠጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀጽ 26

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክትል ሊቀመንበር ተግባርና ሀላፊነት

1. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሊቀ-መንበር በማይኖርበት ጊዜ ሊቀመንበሩን ተክቶ ይሰራል።
2. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውና በሊቀ-መንበሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

## አንቀጽ 27

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የቁጥጥር ኮሚሽን አመሰራረት፣ ተግባርና ሀላፊነት እና አሰራር

### የኮሚሽኑ አመሰራረት

2. የኮሚሽኑ ተግባርና ሀላፊነት

   2.1. ኮሚሽኑ የአባል ሊጎችና በጋራ ተቋማት ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ አባላት መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል። በጋራ ኮሚቴዎች አማካኝነት የሚፈፀም የመብት መጣስን በተመለከተ የሚቀርብለትን ቅሬታዎች ተቀብሎ ያጣራል። የራሱን የውሳኔ ሃሳብም ያሳልፋል።

   2.2. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ንብረትና ገንዘብ በትክክል መያዙንና በተቀመጠለት የአሰራር ስርዓት መሰረት ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል።

በዚህ ረገድ የሚታዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል የሚያስችል የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

2.3. ኮሚሽኑ በ2/3 ድምጽ አስቸኳይ ጉባኤ መጠራት አለበት ብሎ ካመነና ከኢህአዴግ ወጣት ሊግ ቋሚ ጉባኤ አባላት 1/3ኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ጉባኤ እንዲጠራ ያደርጋል፡፡

2.4. ኮሚሽኑ ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ከኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር የሀሳብ አንድነት ከተያዘበት ውሳኔው ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ልዩነት ከተከሰተ ልዩነቱ ወደ ኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት ይተላለፋል፡፡ ምክር ቤቱ የሚያሳልፈው ውሳኔ እስከ ጉባኤ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2.5. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ወይም አባል ሊጎቹን የሚመለከቱ መጣራት የሚገባቸው ጉዳዮች ሲኖሩ በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት ጥያቄ እንደነፃ አጣሪ አካል ሆኖ ያገለግላል፣ ሪፖርቱንም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

2.6. እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ሲኖሩ ከሚመለከታቸው የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ ያስፈጽማል፡፡ ከኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጋር የቅርብ ግንኙነት ይመሰርታል፡፡

2.7. ጥፋት በሚፈፅሙ አባሎቹ ላይ የዲስፕሊን እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡ አባሉን ማገድ ወይም ከስልጣኑ ማውረድ የሚችለው በአባላቱ 2/3ኛ ድምጽ ይሆናል፡፡

2.8. ስለስራው ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጉባኤ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2.9. ኮሚሽኑ ከአባል ሊጎች የቁጥጥር ኮሚሽኖች ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

2.10. ኮሚሽኑ በመካከሉ ሊቀ ምክትል ሊቀመንበርና ፀሀፊ መርጦ ለጉባኤው ያስታውቃል፣

2.11 ኮሚሽኑ ይህን የመተዳሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የራሱን አሰራርና መመሪያዎች ያወጣል::

3. ስለኮሚሽኑ ስብሰባ እና አሰራር፣

3.1የኮሚሽኑ መደበኛ ስብሰባ በየ3 ወሩ ይካሄዳል::

3.2የኮሚሽኑ ሊቀመንበርና ፀሀፊ ቋሚ ፅህፈት ቤት ይኖራቸዋል::ከኮሚሽን ሀላፊነታቸው ጋር የሚጋጩ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ተግባራትን በተደራቢነት አይሰሩም፣

3.3 የፅህፈት ቤቱ አባላት ተግባርና ሀላፊነታቸውን በተመለከተ ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ፣

3.4 ኮሚሽኑ የራሱን ዓመታዊ እቅዶች እያዘጋጀ ተግባራቱን ይመራል፣

## አንቀጽ 28

## የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ጽህፈት ቤት

1. የጽህፈት ቤቱ አመሰራረት

1.1. ሊጉ የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል:: በጽህፈት ቤት ተመድበው የእለት ተዕለት ስራዎችን የሚከታተሉና የሚያስፈፅሙ አመራሮችን በስራ አስፈፃሚ ይመደባል፣ እንደሁኔታው የስራ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል::

1.2. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሊቀመንበር ይሆናል::

2. የጽህፈት ቤቱ ተግባርና ሃላፊነት

2.1 ጽህፈት ቤቱ በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ውስጥ የሚካሄደውን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራዎች፣ የፋይናንስና አስተዳደር ስራ በሃላፊነት ያከናውናል:: የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ሥራዎች ማዕከል ሆኖ ይንቀሳቀሳል::

2.2 የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤትና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ እንዲሁም ወጣቱን የሚመለከቱ ስራዎችን ያቅዳል፣ ያስፈፅማል:: አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል::

2.4. በአባል ሊጎች አማካይነት ለሚካሄደው ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ስራ ድጋፍና አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፤ ስራውን ያስተባብራል።

2.5. በጋራ እንደ ኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚንቀሳቀሱ ስራዎችንና አካላትን በቀጥታ ይመራል።

2.6. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን የእቅድ አፈፃፀም ለወጣቱ ያስተዋውቃል፤ ከወጣቱ ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ምክርቤቱን በመወከል ምላሽ ይሰጣል።

2.7. በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ምክር ቤት የጸደቀውን በጀት ያስተዳድራል፤

2.8. በኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ በሚፀድቅ መመሪያ መሠረት የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ፋይናንስና ንብረት እንዲሁም የጽህፈት ቤቱን ሠራተኞች ያስተዳድራል።

2.9. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

2.10. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከሊቀመንበሩ በሚሰጠው መመሪያና ኢህአዴግ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤.

2.11. የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግን በመወከል ይከሳል ይከሰሳል።

2.12. ስለ ስራው አፈፃፀም ለኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለሊቀመንበሩ ሪፖርት ያቀርባል።

3. የጽህፈት ቤቱ አሰራር

3.1 የጽህፈት ቤቱ ስራ አመራር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል።

3.2 ጽህፈት ቤቱ የስራ አፈፃፀሙን በሚመለከት መደበኛና ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለሊቀመንበሩ ያቀርባል።

3.3 ጽህፈት ቤቱ ከአባል ሊጎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት በአባል ሊጎች ጽህፈት ቤት በኩል ይሆናል።

3.4 የጽህፈት ቤቱ ዝርዝር አሰራር፣ ተግባርና ሃላፊነት አስመልክቶ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

3.5 በጽህፈት ቤቱ የሚመደቡ ሃላፊዎችም ሆኑ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ምደባ በተቻለ መጠን የሁሉም አባል ሊጎችን ተዋጽኦ ከግምት ያስገባ ይሆናል።

## ? ??? ???? አንቀፅ 29

## ማጠቃለያ

## መመሪያ ስለማውጣት

1. የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ ምክር ቤት መተዳደሪያ ደንቡን በስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ የተለያዩ መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፡፡

2. በአሰራር መመሪያዎች በተለይም ለሊጉ ዋና ጽህፈት ቤት በስራ አስፈፃሚ ሊወጣ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 30

## መተዳደሪያ ደንብ ስለ ማሻሻል

1. ከሊጉ ጠቅላላ ጉባኤ በስተቀር ይህን መተዳደሪያ ደንብ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሻሻል ወይም መሻር አይችልም፣

2. በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛ የውሳኔ ድምፅ ይሻሻላል፡፡

## አንቀፅ 31

## የገቢ ምንጭ

1. የሊጉ የገቢ ምንጭ ከአባላት መዋጮ እና ከተለያዩ ደጋፊዎች የሚገኝ ህጋዊ ድጋፎች ይሆናል፡፡ የአባላት መዋጮ አከፋፈል ዝርዝር አፈፃፀም በምክር ቤቱ መመሪያ የሚወጣ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 32

## መተዳደሪያ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

1. ከሊጉ ጠቅላላ ጉባኤ በስተቀር ይህን መተዳደሪያ ደንብ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሻሻል ወይም መሻር አይችልም፣
2. በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛው የውሳኔ ድምፅ ይሻሻላል፣

## አንቀጽ 31

## የገቢ ምንጭ

የሊጉ የገቢ ምንጭ ከአባላት መዋጨ እና ከተለያዩ ደጋፊዎች የሚገኝ ህጋዊ ድጋፎች ይሆናል፡፡ የአባላት መዋጮ አከፋፈል ዝርዝር አፈጻፀም በምክር ቤት መመሪያ የሚወጣ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 32

## መተዳደሪያ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ግንቦት 20/2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡